# መዳን በሐዋርያት ትምህርት ብቻ

1. ሐዋርያት ትምህርታቸው ከኢየሱስ ብቻ እንጂ ፍልስፍና ስላልተቀላቀለበት ከሰማይ ነው። ፩ቆሮ 4፡1-4። ፩ቆሮ 2፡17።

በማቴ 13፡11 ...«ለእናንተ የመንግሥተ ሰማያትን ምስጢር ማወቅ ተሰጥቶአችኋል፣ ለእነርሱ ግን አልተሰጣቸውም»። በማለት ከሐዋርያት ትምህርት (ዶክትሪን) ውጭ የሆነ በሙሉ ከሰማይ የመጣ አለመሆኑን ያረጋግጣል።

በማቴ 23፡7-9 ኢየሱስ ከራሱ በቀር ሌላ መምህር እንዳንቀበል አስጠንቅቆናል። ሐዋርያትን ግን እርሱ ራሱ ስላስተማራቸው፡- እናንተን የሚሰማ እኔን ይሰማል፣ እናንተንም የጣለ እኔን ይጥላል፤ እኔንም የጣለ አባቴን ይጥላል ሲል የተረጋገጠና ልንቀበለውም የሚገባ ትምህርት የሐዋርያት ብቻ መሆኑን አረጋግጦልናል። ሉቃ 10፡16።

2. ሐዋርያት ራሳቸው ብዙ ሐሰተኛ የትምህርት ነፋስ (ዶክትሪን) እንደሚመጣ ሲያመለክቱ፡-

በኤፌ 4፡14 «እንደ ስሕተት ሽንገላ ባለ ተንኮል በሰዎችም ማታለል ምክንያት በትምህርት ነፋስ ሁሉ እየተፍገመገምን ወዲያና ወዲህ እየተንሳፈፍን ሕጻናት መሆን ወደፊት አይገባንም»፣ እያሉ አስጠንቅቀውናል።

በዘመናችን በሰው ፍልስፍና የተፈጠሩ ለቁጥር የሚያስቸግሩ የትምህርት ነፋሶች መኖራቸው ዓይናችን የሚያየውና ጆሮአችንም የሚሰማው እንደ አሸን በየወቅቱ በመፍላት ላይ ይገኛሉ።

3. የቱን ትመርጣለህ? በትምህርት ነፋስ መፍገምገምን? ወይስ የጸናውን የሐዋርያት ትምህርት፤ ተቀብሎ መጽናትን?

4. በ፪ቆሮ 11፡1-4 «ስንመለከት፡- ...ነገር ግን እባብ በተንኮሉ ሔዋንን እንዳሳታት፣ አሳ ባችሁ ተበላሽቶ ለክርስቶስ ከሚሆን ቅንነትና ንጽሕና ምናልባት እንዳይለወጥ ብዬ እፈራለሁ። የሚመጣውም ያልሰበ ክነውን ሌላ ኢየሱስ ቢሰብክ፣(ልዩ ኢየሱስም እንደሚፈለሰፍ ያመለክታል)። ወይም ያላገኛችሁትን ልዩ መንፈስ (መንፈስ ቅዱስ የሚመስል አሳች መንፈስም አለ ማለት ነው)፣ ወይም ያልተቀበላችሁትን ልዩ ወንጌል ብታገኙ፣ በመልካም ትታገሡታላችሁ» ይላል። ዛሬ በዘመናችን አንድ ሃይማኖት መኖር ሲገባው በትም ህርት ነፋስ ምክንያት ከ3000 ሃይማኖቶች በላይ ተፈጥረዋል። ልብ ብለን ወደ ሐዋርያት ኢየሱስ፣ መንፈስና ወንጌል ብናተኩር ለነፍሳችን እረፍትን እናገ ኛለን።

አዳምና ሔዋን በመጀመሪያ ከእግዚአ ብሔር በተሰጣቸው የማይለወጥ ትምህርት አልጸኑም፤ በሰይጣን ውሸታምና አታላይ ትምህርት ተወስደው ሕይወትን አጡ፤ ሞትን፣ ያውም የዘላለምን ሞት አተረፉ አንተስ በየትኛው ዶክትሪን ላይ ነህ?

5. በ፩ጢሞ 4፡1-2 «መንፈስ ግን በግልጥ፡- በኋለኞች ዘመናት አንዳንዶች የሚያስቱ መናፍስትንና በውሸተኞች ግብ ዝነት የተሰጠውን የአጋንንትን ትምህርት እያዳመጡ፣ ሃይማኖትን ይክዳሉ» ሲል ጳውሎስ ተንቢዮአል። ከሐዋርያት ትምህርት ውጭ የሆነ ዶክትሪን ሁሉ በአጋንንት የተፈ ለሰፈ መሆኑን ያረጋግጣል።

6. ኢየሱስ ራሱ፡- በማር 7፡6-7 ስለ ሰው ሰራሽ ሃሰተኛ ትምህርት ሰርጎ መግባት ሲገልጥ፡- «...ይህ ሕዝብ በከንፈሩ ያከብረኛል ልቡ ግን ከእኔ በጣም የራቀ ነው። የሰውም ሥርዓት የሆነ ትምህርት እያስተማሩ በከንቱ ያመልኩኛል» በማለት በሰው የተፈ ለሰፈ ዶክትሪን ይዞ አምላክን የሚያመልክ ሁሉ በከንቱ! እየደከመ እንዳለ ባለቤቱ ኢየሱስ አስረግጦአልና ወዴት ነህ?

የመዳን መንገድ የመያዝ ጊዜው (ጨለማው ሳይበረታ) አሁን ነው።

7. በ፪ነገ 17፡24-33 ያለውን ታሪክ ስንመለከት፡- ከሶርያ ወደ እስራኤል ወደ ሰማርያ የመጡት አሕዛብ የአገሩን አምላክ ወግ ወይም ዶክትሪን ባለማወቃቸው ጠንቅ አንበሶች ስለገደሉዋቸው፣ የአሶር ንጉሥ አስተዋይ ሰው ስለነበረ የእግዚአብሔርን ትምህርት የሚያስተምር ካህን በመላክ እንጂ በሌላ ኃይል አንበሶችን ማቆም እንደማይቻል ተረድቶ፣ ሕዝቡን አዳነ። እኛስ? አንተስ? ዛሬ ከዘላለም ሞት አንበሳ የምንድነው በሐዋርያት ዶክትሪን ብቻ እንደሆነ አውቀሃል ወይ?

8. በሮሜ 6፡18 «...ለተሰጣችሁለት ለትምህርት ዓይነት ከልባችሁ ስለታዘዛችሁ» በማለት የትምህርት ወይም የዶክትሪን ዓይነት ለኩነኔም ሆነ ለጽድቅ ወሳኝ መሆኑን ያረጋግጥልናል። አንተ የያዝከው የዶክትሪን ዓይነት ወዴት የሚመራ ነው?

9. በኢየሩሳሌም ከተማ፣ የጸሐፍት፣ የፈሪሳውያንና የሰዱቃውያንም ትምህርቶች ወይም ዶክትሪኖች ነበሩ፤ ዳሩ ግን የሐዋ ርያት ትምህርት ብቻ አሸንፎ ኢየሩሳሌምን እንደሞላበጣት ተጽፎአል። የሐዋ 5፡28

10. ሐዋርያው ጳውሎስ፣ በገላትያ የነበረውን የአይሁድ ማሕበር ወደ ኦሪት ሥርዓት እና ወንጌልን ወደማጣመም ስለተ መለሱ፡ «በክርስቶስ ጸጋ እናንተን ከጠራ ችሁ ከእርሱ ወደ ልዩ ወንጌል እንዲህ ፈጥናችሁ እንዴት እንዳለፋችሁ እደነቃለሁ፤ እርሱ ግን ሌላ ወንጌል አይደለም፤... ነገር ግን እኛ ብንሆን ወይም ከሰማይ መልአክ፤ ከሰበክንላችሁ ወንጌል የሚለይ ወንጌልን ቢሰብክላችሁ፣ የተረገመ ይሁን» አለ ይላል። ይህን መርገም ንቀው በፍልስፍና ወደተመ ሠረተው የትምህርት ነፋስ የተወሰዱ እጅግ ብዙ ናቸው። ገላ 1፡6-12 ተመልከት። ከዘላ ለም መርገም ለመዳን ወደ ሐዋርያት ወንጌል ለመመለስ ጊዜው አሁን ነው።

11. በዕብ 13፡8-9 «ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትና ዛሬ እስከ ለዘላለምም ያው ነው" ልዩ ልዩ ዓይነትም በሆነ በእንግዳ ትምህርት አትወሰዱ ልባችሁ በጸጋ ቢጸና መልካም ነው እንጂ በመብል አይደለም፤ በዚህ የሚሠሩበት አልተጠቀሙበትምና» በማለት እንግዳ ትምህርት ወይም ዶክትሪን የሆድ መደለያ ሳይዝ እንደማያስት ያረጋግጣል የእግዚአብሔር መንግሥት መብልና መጠጥ አይደለችም። ጽድቅና ሰላም በመንፈስ ቅዱስም የሆነ ደስታ ናት እንጂ። ሮሜ 14፡17።

12. በፊልጵ. 3፡2 «ከውሾች ተጠበቁ፣ ከክፎችም ሠራተኞች ተጠበቁ፣ ከሐሰተኛም መገረዝ ተጠበቁ። እኛ በመንፈስ እግዚአብሔርን የምናመልክ በሥጋም የማንታመን እኛ የተገረዝን ነንና»። በማለት ከሐዋርያት ውጭ የሆነ ትምህርት ተናካሽና ክፉ መሆኑን እንጂ በመንፈስ ቅዱስ የማያመልክ መሆኑን ያረጋግጣል።

13. በ፪ጢሞ 4፡1-4 በእግዚአብሔር ፊት በሕያዋንና በሙታንም ሊፈርድ ባለው በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ፊት፣ በመገለጡና በመንግሥቱም እመክርሃለሁ፣ ቃሉን ስበክ፣ በጊዜ ውም አለጊዜውም ጽና... ሕይወት የሚገኝበትን ትምህርት የማይታገሱበት ዘመን ይመጣልና፤ ነገር ግን ጆሮቻቸውን የሚያሳክክ ስለሆነ፣ እንደገዛ ምኞታቸው ለራሳቸው አስተማሪዎችን ያከማቻሉ። እውነትንም ከመስማት ጆሮቻቸውን ይመልሳሉ፣ ወደ ተረትም ፈቀቅ ይላሉ። አንተ ግን ነገርን ሁሉ በልክ አድርግ፣ መከራን ተቀበል፣ የወንጌል ሰባኪነት ሥራ አድርግ፣ አገልግሎ ትህን ፈጽም።" ይልሃል። እንዲህ ያለ ከባድ ማስጠንቀቂያ ሊያሰማን ያስገደደው፦ የሐዋርያትን ትምህርት ሊለውጡ የተዘጋጁ የአጋንንት መንፈሶች እንዳሉ ስለታየውና እነዚህ መናፍስትም ፍልስፍናንና ተረትን ወደ ሰው ልብ በማስተዋል ለውጥን ለንጊዜው የማድረግ ኃይል እንዳላቸው ያስረግጣል። አንባቢ ሆይ! በማስተዋል ቃሉን ተመልክተውና በየትኛው አካባቢ እንዳለህ መርምር። የነፍስ መዳኛ መንገድ ወይም ሃይማኖት አንዲት እንጂ 3000 ሊሆን አይችልም። ፈጥነህ መጽሐፍ ቅዱስን ከጻፉት ሐዋርያት ጋር ተስማማ።

14. የያዕቆብ ወንድም ይሁዳ በመልዕክቱ፦ «ወዳጆች ሆይ፣ ስለምንካፈለው ስለመዳናችን ልጽፍላችሁ እጅግ ተግቼ ሳለሁ፣ ለቅዱሳን አንድ ጊዜ ፈጽሞ ስለተሰጠ ሃይማኖት እንድትጋደሉ እየመከርኋችሁ እጽፍላችሁ ዘንድ ግድ ሆነብኝ። ከብዙ ጊዜ በፊት ለዚህ ፍርድ የተጻፉ አንዳንዶች ሰዎች ሾልከው ገብተዋልና፤ ኃጢአተኞች ሆነው የአምላካችንን ጸጋ በሴሰኝነት ይለውጣሉ፣ ንጉሣችንንና ጌታችንንም ብቻውን ያለውን ኢየሱስ ክርስቶስን ይክዳሉ»።

ዳሩ ግን ሁሉን አንድ ጊዜ ፈጽሞ ምንም የተማራችሁ ብትሆኑ ጌታ ከግብጽ አገር ሕዝቡን አድኖ የማያምኑትን በኋላ እንዳጠፋቸው ላሳስባችሁ እወዳለሁ» በማለት ለሐዋርያት አንድ ጊዜ ፈጽሞ የተሰጠ ምንም ጉድለት የሌለው ትምህርት መሆኑን ያረጋግጣል። (ይሁዳ ቁ. 3-5)

15. ቲቶ 1፡9፦ «ሕይወት የሚገኝበት ትምህ ርት» ይለዋል።

ቲቶ 2፡1፦ «አንተ ግን ሕይወት ለሚገኝበት ትምህርት የሚገባውን ተናገር» ይላል።

ሁሉን አንድ ጊዜ ፈጽሞ ቢማሩትም ትመህርትን ለመለወጥና በትምህርት ነፋስ ለመፍገምገምና ለመንሳፈፍ የሚከጅሉትን ማዳን ፈጽሞ የማይቻል ነው። ለሥጋዊ ጥቅማቸው የክርስቶስን እውነት ይሸጡታልና። ሮሜ 16፡17-20። ፊል 3፡17-21።

ከኢዮርብአም ስህተት መዳን ከጊያዝም ጥማት መራቅ የጥበብ መጀመሪያ የሆነውን እግዚአብሔርንና ትምህርቱን ገንዘብ ማድረግ ከዘላለም ሞት ያድናል። ይሁዳ ክርስቶስን የሸጠው እውነትን አጥቶ ... በረም፣ የኒቆላውያን መንፈስ እና የገንዘብ ፍቅር ስለነበረበት ነው። የሐዋ.ሥራ 6። ራእይ 2፡13-17።፪ነገስት 5።

፪ጢሞ 3፡16-17 የእግዚአብሔር ቃል «ለትምህርትና ለተግሣጽ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል» ይላል። ሐዋ.ሥራ 2፡42። ፪ዮሐ 9። ሮሜ 16፡17-20። «ነገር ግን፣ ወንድሞች ሆይ እናንተ የተማራችሁትን ትምህርት የሚቃወሙትን፣ መለያየትንና ማሰናከያን የሚያደርጉትን ሰዎች እንድትመለከቱ እለምናችኋለሁ፣ ከእነርሱ ዘንድ ፈቀቅ በሉ፣ እንዲህ ያሉት ለገዛ ሆዳቸው እንጂ ለጌታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ አይገዙምና፣ በመልካምና በሚያቆላምጥ ንግግርም ተንኮል የሌለባቸውን ሰዎች ልብ ያታልላሉ... የሰላ ምም አምላክ ሰይጣንን ከእግራችሁ በታች ፈጥኖ ይቀጠቅጠዋል። የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ከእናንተ ጋር ይሁን»።

## ለተጨማሪ ማብራሪያ

Apostolische Pfingstgemeinde
Friedelsheimerstr. 18-20
D - 68199 Mannheim (Neckarau) /Germany
Pastor Raymond Wey
Assistent Pastor Sascha Wey
www.jesus-is-god.de